የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

ቀን/Date: ታሕሣስ 09 2013
ቁጥር / Ref: ወ2/ሰ/124.1 / 8641 /2013

ለሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
ለሁሉም የምርምር ተቋማት
ለሁሉም የሙያ ማህበራት
<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ:- <u>እውቅና ያገኙ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታተሙ የምርምር ጆርናሎችን ስለማሳወቅ</u>

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1097/2011 በተሰጠው ሀገራዊ የሳይንስ ስራዎችን የማስተባበርና የመምራት ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታተሙ የምርምር ጆርናሎችን ጥራት ለማሳደግ እና ከዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ደረጃ እንዲኖራቸው ለማድረግ "ብሄራዊ የምርምር ጆርናሎች ምዘና እና እውቅና አሰራር ስርዓት" በመዘርጋት ከመስከረም ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ስራ መግባቱ ይታወሳል፡፡

በዚህም መነሻ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 01/2012 እና 02/2012 መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ በ2012 ዓ.ም የምርምር ጆርናል የእውቅና ግምገማ ጥሪ ተላልፎ የ34 ጆርናል አሳታሚዎች ቀርበዋል፡፡ በተዘጋጀው የምርምር ጆርናሎች የግምገማ መስፈርት መሰረትም ሰነዶቹ በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ተገምግመው ከዚህ በታች የተዘረዘሩ 16 ጆርናሎች የግምገማውን መስፈርት ስላሟሉ እውቅና ያገኙ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

1. ባህርዳር ጆርናል ኦፍ ኤዱኬሽን
2. ኢስት አፍሪካ ጆርናል ኦፍ ሳይንስ
3. ኢስት አፍሪካ ጆርናል ኦፍ ሶሻል ሳይንስ ኤንደ ሁማኒትስ
4. ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ አግሪካልቸራል ሳይንስ
5. ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ አፕላይድ ሳይንስ ኤንደ ቴክኖሎጂ
6. ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ ኤዱኬሽን
7. ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ እኮኖሚክስ
8. ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ ሄልዝ ደቨሎኘመንት
9. ኢትዮጵያን ጆርናል ኦፍ ሶሻል ሳይንስ ኤንደ ላንጉዌጅ ስተዲስ
10. ኢትዮጵያን ሪሰርች ጆርናል ኦፍ ሶሻል ሳይንስ ኤንደ ሁማኒትስ
11. ሀራማያ ሎው ሪቪው
12. ጆርናል ኦፍ ዘድራይላንድ
13. ጆርናል ኦፍ ኢትዮጵያን ስተዲስ
14. ጅማ ዩኒቨርሲቲ ጆርናል ኦፍ ሎው
15. ሚዛን ሎው ሪቪው
16. ኦሮሚያ ሎው ጆርናል

በመሆኑም ጆርናሎቹ በቀጣይ አመታት የጥራት ደረጃቸውን እያሳደጉ እንዲሄዱ የሚኒስቴር መ/ቤታችን ድጋፍ የማይለያቸው መሆኑን እየገለፅን ሌሎች በሀገራችን ተቋማት የሚታተሙ ሳይንሳዊ ጆርናሎችም ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ በተዘረጋው የእውቅና ግምገማ ስርዓት መሰረት ለጥራት እንዲሰሩ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Science and Higher Education

ሙኤል ኡርቃቶ ኩርኬ (ፒኤችዲ)
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ:-</u>
- ለኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ
- ለከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ
- ለከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡራን ሚኒስትር ዴኤታዎች ጽ/ቤቶች (3)
- ለሳይንስና ምርምር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
- ለተቋማት ትስስርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
- ለከፍተኛ ትምህርት አካደሚክ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
- ለኢቴርኔት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
- ለአስተዳደርና መሰረተ ልማት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
- ለምርምርና ስርፀት ዳይሬክቶሬት
  <u>ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር</u>